


# ትታያለሽ

*ሥርጉተ ሥላሴ*

ታበሪያለሽ
ታስውቢያለሽ
ብርቴ ሀቅን ታነጥሪያለሽ።

ታፅናኛለሽ
ትራሪያአለሽ
ትመክሪያአለሽ
ብርቴ ለእኛ ታፅነቢያለሽ።

ጥንከሬ ታመርቻለሽ
ታሪካችን ትፈጥሪያለሽ
ሴትነትን ታስውቢያለሽ …
ጀግንነትን ታኅያለሽ!

ምሰሶአችን …
ባላችን ነሽ ወጋግራችን …
መመኪያችን
ዋቢያችን ነሽ …
ለእኛ ብለሽ ትቀልጫለሽ
ፍፁም ልቀሽ ትታያለሽ።

*ሥጦታ፣ ለክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚዲቅሳ ለአንድነት ሊቀመንበር*
*የካቲት 24 ቀን 2001 ዓ.ም ጀርመን*